# <u>ከሕዝብ ጀርባ የሚካሄድ ሁሉ መጋለጡ አይቀርም</u>

<u>መኮንን ተ. ደምሴ</u>

ከሰው ስህተት አይጠፋም ነውና የቅንጅት ደጋፊ ሆኜ፤ በዚህ አውሬ ሀገርም ለፍቼ ካገኘኋት የአቅሜን አዋጥቼ በመቆየቴ ፀፀት የለኝም፡፡ አመራሬ ካልኳቸው ግን የምጠብቀው ነበረኝ፡፡ የቅንጅቱን አላማና አቅዋም ማራመድ፤ ለአባላት ግልፅ መሆን፤ ደጋፊን አለማደናገር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ቅንጅት ፈጠር የተባለው ትብብር ሰማይ ምድሩን ገልብጠብናል ብል ስህተት አይመስለኝም፡፡ በግል ባላውቃቸውም ሰነዱን በቅንጅት ስም ፈረሙ ስለተባሉት ግለሰቦች በየዌብ ሳይቱ የተፃፈውን ሳነብና ስራቸውንም ሳይ በእወነትም ቅንጅቱን ይወክላሉ ማለቱ ከብዶኛል፡፡ አቶ ሰለሞን በቀለ ደግሞ በእሁዱ የዋሺንግተን ስብሰባ ይህን አርማጃ የወሰድነው በራሳችን ነው ከማለታቸው በተጨማሪ እኛም እንደታሰሩት መሪዎች የመወሰን መብት አለን ያሉት ደግሞ ይበልጥ ጥርጣሬዬን አባብሶታል፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ለዓመታት ሲየስተጋቡ የነበራቸውን አቅዋም ገልብጠው የኦነግም የኤርትራም ደጋፊ አቅዋም መያዛቸው በጣም አስገርሞኛል፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ግን የቅንጅት አቅዋም ግልፅ ነው፡፡ የሰብዓዊ መብት ታጋዩ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ደጋግመው ገልፀውት እንድነበረው ቅንጅቱ ከህብረቱ ጋር በሚገባው ደረጃ ተጣምሮ ለመስራት እንቅፋት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ህብረቱ የጎጥ ድርጅቶችንም ያቀፈ ስለነበረ ነው፡፡ ቅንጅትም ሆነ ፕሮፌሰር ጌታቸው የጎጥ ድርጅቶችን ሲቃወሙ ወይም በሩቁ ሲሉ የነበሩ ናቸው፡፡ ዛሬ ምን የአቅዋም ለውጥ ተደርጎ ነው ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር የቅንጅት ተጠሪዎች ነን የሚሉት የሚፈራረሙት? ፕሮፌሰር ጌታቸው በፃፉት የመከላከያ ፅሁፍ ደፈረኝ ባይሉ ሊያደናግሩን እየጣሩ ናቸው እንጂ ያብራሩት የለም፡፡ በዋሺንግተኑ የእሁዱ ስብሰባም ቢሆን ኦነግ የአቅዋም ለውጥን አንፀባርቆ አልታየም የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሰነዱን የፈረሙት ሆኑ ፕሮፌሰርም በኤርትራ ላይ የአቅዋም ለውጥ በዱብ ዕዳ መልክ አሰምተውናል፡፡ ኤርትራ በእህት ሀገር ወይም በጎረቤት ሀገርነት ተቀምጣለች፡፡ ይህ አቅዋም መቸ ነው የቅንጅት የሆነው? አባላትስ የሀገር ቤት መሪዎቻችንስ ይህን ያውቃሉ ወይስ እነ አቶ ሰለሞን በቀለ በራሳቸው ጉልበት ነው ለሻዕቢያ እውቅናን የሰጡት?

የምንታገለው በሰላም ነው ተብሎ የተከፈለው መስዋዕትነት ቀላል አይደለም፡፡አንዳንዶቻችን ይህ መንገድ እስከመቼ ብለን ብናጉረመርምም የድርጅታችንን ፖሊሲ ተከትለን ቀጥለናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ አረመኔው ወያኔ ወገኖቻችንን የቅንጅት ደጋፊ ብሎ ጨፍጭፎና አስሮ፤ መሪዎቻችንን አስሮ እያለ ከመለስ ዜናዊ ጋር በአዲስ አበባ በጋራ ተቀምጠን እንደራደራለን ተብሎ በአቶ ሰለሞን የተነገረው ቢያንስ ግራ አጋብቶናል፡፡ ብዙ ደጋፊዎች ከዚህ የአሁኑ ሂደት በስተጀርባ ምን የተሸረበ ሴራ አለ ብለው መጠየቅ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ የሀገራችንን አኩሪ ታሪክ በመቶ ዓመት ሲወስንስ የቅንጅት መሪዎች የዚህ ሀሰት ተባባሪ ለምን መሆን ተገደዱ---ምን አዲስ ነገር መጣ? በግርግሩ መሪዎቻችን ለከፋ አደጋ ይጋለጡ ይሆን ብለንም ሰግተናል፡፡ ሻለቃ ዮሴፍ ለአንድ የዲሲ ራዲዮ በሰጡት መግለጫ ከእነ ኦነግ ጋር ከአምስት ዓመት በፊት የጀመርነው ግንኙነት ነው ሲሉ (ከአምስት አመት በፊት ቅንጅት ነበረ ለመሆኑ?) አቶ ሰለሞንና ዶክተር ስዩምም ግንኙነታችን ከአራት ዓመት በፊት የጀመረ ወይም የነበረ ግንኙነት ነው ያሉት/ያኔስ ቅንጅት ነበር ማለት ቢቀር እንኳን/ መሪዎቻችንን አስሮ በሽብርተኝነት በተለይም ከኦነግና ሻዕቢያ ተመሳጥረዋል ብሎ ለሚከሰው ወያኔ ጠቃሚ መረጃ መስጠት መሆኑ ይታያል፡፡ አሰቡትም አላሰቡትም ማለቴ ነው፡፡ ይህስ ለምን ተደረገ ብለን መጠየቅ ተገደናል፡፡

ለጠላት ክፍተት ላለመስጠት ብለን መጠየቅ የሚገባንን ሳንጠይቅ ቆይተናል፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሆኑ የእሁዱ መድረክ ተናጋሪዎች በቂ ምላሽ አልሰጡም፡፡ በእውነቱ ሊያደናግሩን ከመሞከር ባሻገር፡፡ ወያኔ አልቆለታል፤አሜሪካን ከእኛ ጋር ነው የሚባለውን ቢያንስ

የአሜሪካው ባለስልጣን ያማሞቶ በአዲስ አበባ እያለ ካለውም የሚገጠም ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በፍለስፍናና ሎጂክ ስንማር ኖን ሴክዊቱር የሚባል ነገር ትዝ ይለኛል፡፡ የፕሮፌሰር ጌታቸውም የገለፃ ሙከራ ያን መሰለኝ፡፡ ትብብሩ ላይ ጥያቄ ስናነሳ ቅንጅትና ኦነገ ቢቀራረቡ አይሻልም ብለው በመልስ መልክ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ጥያቄው አይደለም፡፡ በደፈና መቀራረብን የሚቃወም የለም፡፡ ጥያቄወ በምን መሰረት፤ለምን ዓላማ የሚለው ነው፡፡ ከኦነግ መቀራራብ የተባለው ቅንጅትን በኦነግ መዳፍ ስረ ማስገባት ወይም የቅንጅትን መሰረታዊ እምነቶች መሻር ከሆነ መቀራራቡ ከቶም አይጠቅምም፡፡ ተመሰረተ የተባለው ትብብር ኢትዮጵያዊነትን እንኳን የማያስረግጥ ነውና ይህ ቅንጂታዊ አቅዋም ሊባል አይቻልም፡፡ ከመለስ ዜናዊ ጋር--ያውም የፖለቲካ እስረኞችን ባልፈታበትና የሕዝብን ድመፅ አለካብር ብሎ ባለበት-- አዲስ አባባ ሄዶ መደራደር የቅንጅትን ዓላማ የሚየራምድ ሳይሆን የሚጎዳ ነው፡፡ ድርደሩ በወያኔ ቁጥጥር ስር፤ በመለስ ዜናዊ ህገ መንግሰት ስር ነውናም ፋይዳ ቢስ መሆኑ ከዛሬ እንኳን ሊነገር የሚችል ነውና የት ላይ ነው ቅንጅቱ ከትብብሩ የሚጠቀመው?

ሁሉን እንቅ ባንልም የምንደግፈው ድርጅትወ መሰረታዊ አቅዋሙን ሲቀይር መነገር ነበረብን፡፡ መቸ ጉባዔ ተካሄደ? መቸ መሪዎቻችን ድምፃቸውን አሰሙ? በበኩሌ እነ ሰለሞን በቀለን ተከትዬ ገደል ለመግባት ዝግጁ አይደለሁምና (መገልበጫ ንዋይም አላከበትኩምና) ሁሉም የቅንጅት አባሎችና ደጋፊዎች የተፈፀመውን ከባድ ስህተት በአስቸኳይ ለማረም እንዲነሱ ጥሪ አስተላልፋለሁ፡፡